የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ

ከታህሳስ 5 እስከ 11፤2017 ዓ.ም
DEC 14-20, 2024 G.C

## 1.ብሔራዊ ባንክ ዲጂታል ገንዘብን በሚመለከት መመርያ ሊያወጣ እንደሚችል አስታወቀ

**ሪፖርተር: December 18, 2024**

የበርካታ አገሮች የማዕከላዊ ባንኮች ጥሬ ገንዘብ ትተው ወደ ዲጂታል ገንዘብ (Currency) እየተሸጋገሩ መሆኑን የገለጸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በኢትዮጵያም እንደ አስፈላጊነቱ ይኼንን የተመለከተ መመርያ ሊያወጣ እንደሚችል አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ረቂቁ አዋጅን አስመልክቶ የፕላን በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበው አዋጅ ቁጥር 1359/2017 ትናንት ማክሰኞ ታኅሳስ 8 ቀን 2017 ዓ.ም. ሲፀድቅ ነው የተገለጸው፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በተለይ የክሪፕቶ ከረንሲ ወይም የዲጂታል/ኤሌክትሮኒክ ገንዘብ በመጠቀም ክፍያ ከመፈጸም ጋር ተያይዞ ያለውን የአዋጁን ድንጋጌ በማንሳት፣ ብሔራዊ ባንክ ይህንን እንዴት ሊቆጣጠረው ይችላል? ቴክኖሎጂውስ አገሪቱ ላይ አለ ወይ? አፈጻጸሙስ ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎችን ለብሔራዊ ባንክ ገዥ አቅርበው ነበር፡፡

በተለይ ፈትሒ ማህዲ (ዶ/ር) የተባሉ የምክር ቤት አባል የአዋጁን አንቀጽ 37/1 በመጥቀስ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ብሔራዊ ባንክ ካልፈቀደ በስተቀር ክሪፕቶ ከረንሲ ወይም ማንኛውም ሌላ ዲጂታል/ኤሌክትሮኒክ ገንዘብ በመጠቀም ክፍያ መፈጸም አይቻልም የሚለው ድንጋጌ ጥሩነት አንስተው፣ ነገር ግን አፈጻጸሙ እንዴት ነው? ብሔራዊ ባንክ እንዴት ነው ሊቆጣጠር የሚችለው? የሚለውን በተመለከተ ዝርዝር ነገር የለውም ብለዋል፡፡
https://www.ethiopianreporter.com/136513/

## 2. ብሔራዊ ባንክ የቢትኮይን ኢንቨስትመንት ቁጥጥር ላይ እየመከረ እንደሚገኝ አስታወቀ

**ሪፖርተር :December 15, 2024**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቅርቡ ኢትዮጵያ 55 ሚሊዮን ዶላር ገቢ እንዳገኘችበት የተገለጸውን የቢትኮይን ማይኒንግ ጨምሮ፣ አጠቃላይ ኢንቨስትመንቱን በተመለከተ የቁጥጥር ዘዴው ምን ሊሆን ይገባል የሚለውን እየመከረበት እንደሆነ አስታወቀ፡፡

በሞሮኮ ካዛብላንካ በተካሄደው ዓመታዊው የአፍሪካ ፋይናንሺያል ሰሚት (Afica Financial Summiit-AFIS-2024) የተሳተፉት የብሔራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ ምሕረቱ እንዳስታወቁት፣ በዚህ ወቅት ከቻይና በመቀጠል የክሪፕቶ ማይኒንግ ኢንቨስትመንት ዋነኛ መዳረሻ የሆነችው አገር ኢትዮጵያ ሆናለች፡፡

ቢትኮይንን በተመለከተ ጉዳዩ በሁለት መንገዶች እንደሚታይ ለተሳታፊዎቹ የገለጹት አቶ ማሞ፣ በኢትዮጵያ በርካታ የኢንዱስትሪው ተዋንያን (Players) እንደሚገኙ፣ በአሁኑ ወቅትም ማዕከላዊ ባንኩ የቁጥጥር አካሄዱን እያጤነ እንደሚገኝና ሕጋዊ መሠረት ለመፍጠር እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ተናግረዋል።

‹‹የቁጥጥር ጉዳዩን በተመለከተ እያየነውና እየተመለከትን ነው፣ ነገር ግን አካሄዳችን በግልጽ ሕጋዊ መሠረት በማኖር ማዕከላዊ ባንኩ የመቆጣጠር አቅም እንዲኖረው ይደረጋል፤›› ሲሉ የብሔራዊ ባንክ ገዥው አስረድተዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/136422/

## 3. ኢትዮጵያ በጥራጥሬና ቅባት እህሎች ምርት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነቷን እያሳደገች ነው

**ኢዜአ: ታህሳስ 10/2017**

ኢትዮጵያ በጥራጥሬና ቅባት እህሎች ምርት አቅርቦት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነቷን እያሳደገችና በዘርፉ ያላትን ገጽታ እየገነባች መምጣቷን የኢትዮጵያ ቅባትና ጥራጥሬ እህሎች ማህበር አስታወቀ፡፡
በጥራጥሬና የቅባት እህሎች ኢንቨስትመንት ዙሪያ ያተኮረ ምክክር ዛሬ ተካሂዷል፡፡በምክክሩ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ ያስሚን ወሐብረቢን ጨምሮ የተለያዩ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች፣ ላኪዎች እና ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል፡፡የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ ያስሚን ወሐብረቢ በዚሁ ወቅት መንግስት ለግብርናው ዘርፍ የሰጠው ትኩረት ከፍተኛ ውጤት እንዲመዘገብ ማስቻሉን ጠቅሰዋል፡፡ግብርናን ለማሳለጥ የሚረዱ አስቻይ ፖሊሲዎችን በመቅረጽ ተግባራዊ መደረጉ በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችንና ማነቆዎች መፍታት ማስቻሉን አስረድተዋል፡፡

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5658745

## 4. በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የግል ዘርፉ በብረት ኢንዱስትሪ ተኪ ምርት ላይ እንዲሳተፍ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል - ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ

**ኢዜአ: ታህሳስ 10/2017**

በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የግል ዘርፉ በብረት ኢንዱስትሪ ተኪ ምርት ላይ በስፋት እንዲሳተፍ ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ ገለጹ። ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩና ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በቢሾፍቱ ከተማ የብረት ኢንዱስትሪ መንደር የሚገኘውን የስቲሊ አር ኤም አይ የብረታብረት ማምረቻ ፋብሪካን ጎብኝተዋል። በዚህ ወቅት እንዳሉት፥ ፋብሪካው ከዚህ ቀደም በየቦታው ይጣሉ የነበሩ ቁርጥራጭ ብረቶችን በመጠቀም የአርማታና ሌሎች ብረቶችን በማምረት ላይ መሆኑን ተመልክተናል ብለዋል።

## 5. የፋይናንስ ዘርፉን ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት ያደረገው አዋጅ

**Ethiopian press: December 19, 2024**

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከትናንት በስቲያ በአካሄደው 11ኛ መደበኛ ስብሰባው የፋይናንስ ስርዓቱን ለማሳለጥ የሚያግዝ የብሄራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅን እንዲሁም የውጭ ባንኮች በሀገር ውስጥ ገብተው እንዲሰሩ የሚፈቅደውን የባንክ ሥራ ረቂቅ አዋጅን መርምሮ አጽድቋል፡፡ የብሄራዊ ባንክ አዋጁ በሙሉ ድምጽ፣ የባንክ ሥራ አዋጁ በሶስት ታቃውሞ በአብላጫ ድምጽ ጸድቀዋል፡፡

አዋጁ የኢትዮጵያን የቆየ ማዕከላዊ ባንክ አሰራር ከሌሎች ማዕከላዊ ባንኮች አሰራር ጋር እኩል እንዲጓዝ እንዲሁም የማዕከላዊ ባንኩን አሰራር ዘመናዊ የሚያደርግ እና በሕግ፣ በአዋጅ እና በሕገመንግስት ለሕዝቡ የተሰጡትን ኃላፊነቶች በብቃት መወጣት የሚያስችል አውድ ይፈጥራል።

https://press.et/?p=143315

**6. Ethiopia Moves Closer to an Inclusive Digital Future with Five-Year Strategy**

**ENA: December 18/2024**

Ethiopia is charting a path towards a digitally inclusive future with the rollout of its five-year strategy, designed to bridge technological gaps and ensure equitable access to digital resources for all citizens, including underserved communities.

A Social Dialogue on an Inclusive and Transformative Digital Strategy was held in the capital today, co-organized by Ethiopia's Ministry of Innovation and Technology (MINT) and the International Labour Organization (ILO), with funding from the Dutch government.

The event brought together key stakeholders, including government officials, workers' unions, and employer associations, to validate Ethiopia's five-year national digital inclusive strategy.

The State Minister of Innovation and Technology, Dr. Yeshrun Alemayehu, highlighted the transformative potential of digital technologies for Ethiopia's growth and inclusion. The digital revolution is reshaping our industries, societies, and the way we live and work today, He noted, emphasizing the need to bridge the digital divide.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5651332

**7. Commitment to Quality Cornerstone for Ethiopia's Global Competitiveness: Says President Taye**

**ENA: December 15/2024**

President Taye Atskeselassie emphasized that Ethiopia's commitment to quality is a cornerstone for modernization, prosperity, and achieving global competitiveness. The 11th National Quality Award program, which recognized outstanding manufacturing and service-providing institutions, took place last evening at the Grand Palace.

The President stressed the necessity for Ethiopia's manufacturing and service-providing institutions to adhere to appropriate quality standards.

He highlighted that adhering to and improving quality standards is essential for enhancing the quality of life and achieving the country's development goals.

The president pointed out that Ethiopia's path towards development and global competitiveness is closely linked to sustainable quality improvement.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5631634

**8. Ethiopia's cement production boom raises hopes of construction sector revival**

**Ethiopian Press: December 18, 2024**

The recent shift to a market-based exchange regime has added another layer of complexity, impacting businesses across the board, including the cement industry. Prices and supply chains are feeling the effects, prompting the government to introduce market-based cement pricing. This move allows manufacturers to set their own distribution prices, aiming to stabilize the sector.

Adding a new twist to the market, Lemi National Cement Factory, the largest cement production facility in Ethiopia, has officially entered the scene. Many are now watching closely to see how this new player will influence cement supply and pricing, with expectations that it will bring significant changes to the market dynamics.

https://press.et/herald/?p=107626

**9. Industry Minister Highlights Opportunities of Manufacturing Sector in Ethiopia**

**ENA: December 20/2024**

Ethiopia's Industry Minister Melaku Alebel has highlighted the positive impact of the government's macroeconomic reforms implemented over the past few months in encouraging the manufacturing sector.

The Ministry convened a public-private dialogue today to discuss the opportunities, challenges, and potential solutions for the manufacturing sector in light of recent economic reforms.

Ethiopia has achieved over 816 million USD in import substitution in the past few months after the reform.

Industry Minister Melaku Alebel highlighted the positive impact of the government's macroeconomic reforms.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5661510

**10. Ethiopia's Ambassador Stresses Importance of Leveraging Strong Pan-African Bond**

**ENA: December 16/2024**

The Embassy of Ethiopia in Algeria organized an exclusive event to introduce Ethiopia's world-renowned coffee to Femoca Coffee, one of Algeria's leading coffee importers.

This initiative underscores the deep-rooted political and diplomatic ties between Ethiopia and Algeria, aiming to expand these relations into the economic sphere in line with the objectives of the African Continental Free Trade Area (AfCFTA).

In his opening remarks, Ambassador Muktar Mohamed Ware emphasized the importance of leveraging the strong Pan-African bond between the two sisterly nations to foster robust economic and trade partnerships.

He commended Femoca Coffee for its interest in promoting Ethiopian coffee to Algerian coffee enthusiasts and encouraged direct sourcing from Ethiopia to eliminate reliance on third-party intermediaries.

The Ambassador assured Femoca Coffee of the Embassy's unwavering support in facilitating seamless importation of Ethiopian coffee directly from its source.

The event featured a captivating presentation by the Embassy's coffee expert, highlighting the unmatched quality, rich flavors, and cultural significance of Ethiopian coffee—the birthplace of coffee itself.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5639382